ቤተክርስቲያን አስራትና መስጠት

ሰላም ወገኖች!
የዛሬው የውይይት ርእስ እንዲሆን የፈለግሁት ጥያቄ የሚከተለው ነው፡-

አስራት ምንድን ነው? በአዲስ ኪዳንስ ያለው ተፈፃሚነት እስከ ምን ድረስ ነው?መስጠትስ ምን ማለት ነው?ሁለቱም አንድ ዓይነት ናቸውን?
መፅሐፍቅዱሳዊ በሆነ ምልከታ በመመልከት እስኪ እንወያይባቸው.....ታዲያ ሳንፈራ እንወያይ እሺ? ፖስተሬ እንዳይሰማኝ ብሎ ነገር የለም!
ተባረኩ!
በጌታ እህታችሁ ማህሌት ከቀጠና 2.



3 ዓመታት በፊት በ መንፈሳዊ በ ስም-አልባ የተጠየቀ

?? ?? ????

ጥያቄው ለመወያየትና ለመካከር እስከመጣ ድረስ መለካም ጥያቄ ነው እላለሁ። ተስፋ የማደርገው ክርስትና የገባው ሰው የወንጌሉ ስራ በገንዘብ ካልተደገፈ ሊሰራ እንደማይችል መገንዘብ ይችላል። ስለሆነም የሚንፀባረቁ አቋሞች ሁሉ በትእግስ ቢንሸራሸሩ መልካም ነው እላለሁ። ካልሆነ ግን መስጠት ካልፈለግህ ተወው! ምናምን ብሎ መልስ መስጠቱ ሐሳብ መግለፅን መከልከል ይመስላል። በእርግጥም መፅሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ካልሆነ መስተካከል ያለበት ነገር መስተካከል አለበት። በብሉይ ኪዳን ላይ "ስርቃችሁኛል" ብሎ ሃይለ ቃል ሲጠቀም በአዲስ ኪዳን ደግሞ አንድ ስፍራ ላይ የመበለቶችን ቤት ስለመበዝበዝ ይናገራል። ስለዚህ በአስራት ስም ህግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ማምጣት አይገባም ማለት ይህን ያህል ስሜት መፍጠር የለበትም ብዬ አስባለሁ።

ዳንኤል ከመካኒሳ



3 ዓመታት በፊት በ ስም-አልባ አስተያየት ተሰጥቶበታል

?? ?? ????

3 መልሶች

\+ -

+1 ድምጽ

አሥራት በብሉይ ኪዳን ህግ የተደነገገ አንዱ የህግ ክፍል ነው። እንደ ማንኛውም የብሉይ ኪዳን ህግ ሁሉ ይህ ህግ የተሰጠው ለእስራኤላውያን ብቻ ነው። አሥራት የብሉይ ኪዳን መቅደስ አገልጋዮች ለነበሩ ለሌዋውያን የተሰጠ የርስት ድርሻ ነው። ሌዋውያን እንደ ሌሎቹ የእስራኤል ነገዶች ርስት ስላልነበራቸው የእስራኤል ልጆች አስራት ለእነርሱ ርስት እንዲሆን በህግ ተደንግጓል።
Quote:
ኦሪት ዘኍልቁ
18፥21 ለሌዊም ልጆች፥ እነሆ፥ በመገናኛው ድንኳን አገልግሎት ስለሚያገለግሉ፥ የእስራኤልን ልጆች አሥራት ርስት አድርጌ ሰጥቼአለሁ።

እንደማንኛውም ብሉይ ኪዳን ህግ ሁሉ ይህንንም የአስራትን ህግ መጣስ እርግማን ያመጣል።
Quote:

ትንቢተ ሚልክያስ 3
8 ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን? እናንተ ግን እኔን ሰርቃችኋል። እናንተም፦ የሰረቅንህ በምንድር ነው? ብላችኋል። በአሥራትና በበኩራት ነው።
9 እናንተ፥ ይህ ሕዝብ ሁሉ፥ እኔን ሰርቃችኋልና በእርግማን ርጉሞች ናችሁ።

አስራት እንግዲህ በብሉይ ኪዳን ስር ላሉትና በእጅ የተሰራ መቅደስ ለነበራቸው ለእስራኤላውያን የተሰጠ ህግ ነው። ዓላማውም ለመቅደሱ አገልጋዮች ለሌዋውያን ይሆን ዘንድ ነው።

ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ የሰውና የእግዚአብሔር ግንኙነት በሙሴ ሕግ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በቆመው በአዲሱ ኪዳን ነው። በዚያም ከብሉዩ ህግና ከእርግማኑም ሁሉ ተዋጅተናል።
Quote:
ወደ ገላትያ ሰዎች
3፥13 በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤

ስለዚህ በመጀመሪያ መገንዘብ ያለብን እኛ ያለነው በሌላ ኪዳን ውስጥ ነው እንጂ በሙሴ ኪዳን ውስጥ አይደለንም። ስለ ሁለቱ ኪዳኖች መሰረታው መረዳት ከሌለ አስራትንም መረዳት አይቻልም። ስለ ኪዳኖቹ መሰረታዊ መረዳት ለማግኘት [እዚህ በመጫን](#) ማንበብ ይቻላል።

ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ እንግዲህ ኢየሱስም ይሁን የቤተክርስቲያን አገልጋዮች በአስራት ሲተዳደሩ አንድም ቦታ በመጽሃፍ ቅዱስ አንመለከትም። ይህን ስንል ግን ኢየሱስ ፈሪሳውያንን በብሉይ ኪዳን ስር ያሉ ስለሆኑ በህግ የተጻፈውን ዋናውን ነገር እንዲያከብሩ አስራትንም ጨምሮ ተናግሮአል። ይህ ብቻ አይደለም ለምጻሞች ሲፈወሱ ለካህናት በመቅደስ እንዲያሳዩም ተናግሯል። ይህ በብሉይ ኪዳን የታዘዘና በኪዳኑ ስር ላሉ የሆነ ስለሆነ ማለት ነው።

አዲሱ ኪዳን ከተከፈተና (ማለትም ከክርስቶስ ትንሳኤ በኋላ) ቤተክርስቲያን ከተጀመረች በኋላ ግን በአዲሱ ኪዳን ስር ያሉ ሰዎች አንዳቸውም መፈወሳቸውን ለካህን እንዲያሳዩ ወይም አስራት እንዲሰጡ ሲታዘዙ በመጽሃፍ ቅዱስ አንመለከትም።

ይህ አዲስ ኪዳን ነውና ለወንጌል አገልጋዮችም የሚሰጠው ገንዘብ ዓላማውና አሰባሰቡም የተለየ ነው። በቅድሚያ አዲስ ኪዳን ከገንዘብ በፊት ልብን ነው የሚፈልገው። የእግዚአብሔርም ህግ የሚጻፈው በልብ ላይ ነው። ያለን ነገር ይቅርና እኛ ራሳችን የእግዚአብሔር ቤተመቅደስና ማደሪያ ነን። የራሳችን አይደለንም። በዋጋ የተገዛን ነንና እኛም እንሁን ያለን ሁሉ የጌታ ነው።
Quote:
1 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
6፥19-20 ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደ ሆነ አታውቁምን? በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም፤ ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።

ይህ መሰረታዊው የአዲስ ኪዳን መረዳት ሲሆን፤ ወደ ገንዘብ መዋጮ ስንመጣ ደግሞ የገንዘብ መዋጮ በአዲስ ኪዳን ሁለት ዋና ዋና ባህርያት አሉት።

1. በአለማ የሚደረግ ነው

የገንዘብ መዋጮ ያለ ዓላማ እንዲሁ በባንክ ለማስቀመጥ የሚደረግ ስርዓት አይደለም በአዲስ ኪዳን። ለአንድ ዓላማ

ማከናወኛ የሚደረግ ነገር ነው። ዓላማውም ሁለት ነው። አንደኛ ድሆችን በተለይ ቅዱሳን ድሆችን ለመርዳት ነው። ሁለተኛ ደግሞ እየተዘዋወሩ ወንጌልን የሚሰብኩ የወንጌል ሰባኪዎችን ለማገዝ ነው።

Quote:

1 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 16

1 ለቅዱሳንም ገንዘብን ስለ ማዋጣት፥ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደነገግሁት እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ።

2 እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፥ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀንእንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ።

3 ስመጣም ማናቸውም ቢሆኑ የታመኑ የሚመስሉአችሁ ሰዎች ቸርነታችሁን ወደ ኢየሩሳሌም ያደርሱ ዘንድ ደብዳቤ ሰጥቼ እልካቸዋለሁ፤

4 እኔ ደግሞ ልሄድ የሚገባኝ ብሆን ከእኔ ጋር አብረው ይሄዳሉ።

2 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 9

12 የዚህ ረድኤት አገልግሎት ለቅዱሳን የሚጎድላቸውን በሙሉ የሚሰጥ ብቻ አይደለምና፥ ነገር ግን ደግሞ በብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር ይበዛል፤

ከላይ ባለው ክፍል ጳውሎስ የቆሮንቶስ ሰዎች እንደቀናቸው መጠን በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን (እሁድ እሁድ)ገንዘብ እንዲሰበስቡ ሲደነግግ እናያለን። ዓላማውን በቁጥር አንድ ላይ ሲናገር፤ አስራት ስለሆነ ወይም ህግ ስለሆነ ወዘተ ሳይሆን አንድ specific የሆነ ዓላማ ስላለው ነው። ይህም በኢየሩሳሌም ያሉትን ቅዱሳን ለመርዳት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ የወንጌል አገልጋዮች እንዲረዱ በብዙ ቦታ በአዲስ ኪዳን ተጽፎአል።

2. በልግስና እና በደስታ የሚደረግ ነው

በአዲስ ኪዳን የሚሰበሰበው ገንዘብ በዓላማ የሚሰበሰብ ብቻ ሳይሆን በህግና በአስራት የሚሰጥ ሳይሆን ሰው እንደቀናው በፈቃደኝነት በልግስናና በደስታ የሚሰጥ ነው። ምን ያህል መስጠት እንዳለበት በፐርሰንትም ይሁን በሌላ ሁኔታ የተጻፈ ነገር የለም። በፈቃደኝነት በደስታና እንደቀናው መጠን ይስጥ ነው የሚለው።

Quote:

2 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 9

7 እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።

ወደ ሮሜ ሰዎች

12፥8 የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር።

1 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 16

2 እኔ ስመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፥ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀንእንደ ቀናው መጠን እያስቀረ በቤቱ ያስቀምጥ።

ማጠቃለያ

በአዲስ ኪዳን እንግዲህ የሚሰጠው በዓላማ ነው። ዓላማውም ቅዱሰን ድሆችን ለመርዳትና የወንጌልን ሰባኪዎች

ለማገዝ ነው እንጂ በባንክ ለማከማቸት አይደለም። የሚሰጠውም በግድ ወይም በማስፈራራት ወይም በሃዘን ወይም የአስራትን ህግ ለማሟላት ሳይሆን ከልብ በደስታና በልግስና እንዲሁም ሰው እንደ ቀናው ነው። አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን የሚለየውም ትልቁ ነገር አንዱ አዲስ ኪዳን ልብን እንጂ ስርዓት ማሟላትን አይደለም የሚፈልገው።

ነገር ግን የአስራት ህግን ለመፈጸም የሚፈልጉና ራሳቸውን ከአስራት ህግ በታች ለማስገዛት የሚፈልጉ ሁሉ፤ ከአስራት ህጉ ጋር ተያይዞ ከተሰጠውም ከእርግማኑም በታች ናቸው። ከብሉይ ኪዳን ህግ በታች ያሉ ሁሉ ከእርግማኑም በታች ናቸውና። ከህግም አንዱን ለመፈጸም የሚጥሩ ሁሉ ሁሉንም እንዲፈጽሙ ግዴታ አለባቸውና።

Quote:

ወደ ገላትያ ሰዎች 5

1 በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።
2 እነሆ፥ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ። ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም።
3 ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ።
4 በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል።

እኛ ግን በክርስቶስ የሆነንና ክርስቶስ በመስቀሉ ሞት ከህግ እርማን የዋጀን፤ ለቅዱሳን የምንሰጠው የብሉዩን ህግ ፈጽመን እግዚአብሔርን ለማስደሰት አይደለም። ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲሁ በጸጋው እንዳዳነን ሁሉ በውስጣችን ባስቀመጠው ጸጋ በደስታና በልግስና ቅዱሳንን ለመርዳትና ወንጌልን ለማገዝ አብልጠን እንሰጣለን እንጂ። ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ ለራሱ ክብር በውስጣችን የሚሰራው ነው እንጂ ከእኛ አይደለም።

የአዲሱ ኪዳን ጸጋ በመስጠት በኩል ከህጉ ይልቅ እንዴት አብልጦ እንደሚሰራ በመቄዶንያ ሰዎች ላይ ማየት ይቻላል።

Quote:

2 ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 8

1 ወንድሞች ሆይ፥ ለመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋእናስታውቃችኋለን፤
2 በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸውን ባለ ጠግነት አብዝቶአል፤
3 እንደ ዓቅማቸው መጠን ከዓቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመሰክርላቸዋለሁና።
4 ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይለምኑ ነበር፥
5 አስቀድመውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብን አይደለም።



3 ዓመታት በፊት በ ስም-አልባ [የተመለሰ]

?? ?? ???? ??? ? ??? ?? ??

\+ -

0 ድምጾች

ሰላም ወገኖችህ ሰላምችሁ የብዛ። ዛሬ በተቻለኝ መጠን አጠር አድርጌ ልመልስ እሞክራለሁ።

አስራት ምንድን ነው? ለእግዚአብሄር የምንሰጠው ከገቢአችን 1/10 ማለት ነው።

በአዲስ ኪዳንስ ያለው ተፈፃሚነት እስከ ምን ድረስ ነው?
አይ መቸም በዚህ ዘመን ላለን ስለጌታ ምህረት ጌታን አመሰግናለሁ፤ በአዲስ ኪዳን አስራት ተፈጻሚ ነት ለኔ አሳፋሪ ነው። በአዲስ ኪዳን ያልን አማኞች 1/10 ሳይሆን 100% መስጠት ነው የነበረብን እንደነ ሃዋርያት። ሐናንያ እና ሰጲራ ፍርድ በድርስ ሁላችንም በጠፋን ነበር። ልቡን 100% ያልሰጠ ህዝብ 1/10 ከገቢህ ስጥ ቢባል እና

ባይታዘዝ ሊደንቀን አይገባም ነገሩ የልብ ጉዳይ ነው።

መስጠትስ ምን ማለት ነው? መባ(offering)ወይም ቁርባን ከአስራት ውጭ የሚሰጥ በማንኛውን ቀን እና ጊዜ ከልባችን የምንሰጠው ነው ዘጸ 35፡4-5 ።

ሁለቱም አንድ ዓይነት ናቸውን? አይደለሉም። ሁለቱም የተጀመረው ከህግ በፊት ነው የመጀመሪያ አስራት ስጪ አብራሃም ነው የሰጠውም ለሳሌም ንጉስ እና ለእግዚአብሄር ካህን ለመልክ ጼዲቅ ነው ዘፍ 14፡18-20 ለምን ሰጠው? ስለ ባርከው በቻ ።
ሁለትኛውን የምናገኘው በዘፍ 28፡21-22 የያቆብ ስለት ነው።
መባ ወይም ቁርባን (offering) ግን በአቤል እና በቃኤል ነው የተጀመርው።
ታዲያ አስራት እና መባ ለምን ሊውል ይገባዋል? ብለን ብንጠይቅ እና ብንረዳ በደስታ የምንሰጥ አማኞች እንሆናልን።
አስራት መስጠት ያለበት ሙሉ ግዜአቸውን ሰጥተው በአለንበት አጥቢያ ቤ/ክ ለሚያገለግሉ
መተዳደሪያ ልክ እነደ ለዊ ለእነሱም ይህ ድርሻቻው ነው። መባ ለወንጌል ስርጭት ቤ/ክ ከአጥቢያ አልፋ ለምታድርገው outreach እና ለሌላም የሚውል ነው።
ታዲያ ዛሬ በመንፈስ የምን መገብበት ቦታ አስራት አንሰጥም ወይም መባ ዐናገባም ማለት ለጌታ ስራ አልተባበርም ማለት ነው። አማኞች ስንሆን ወይ ለወንጌል ስራ ሀጂ ዎች ነን ውይ ደግሞ ላኪዎች ነን ። አህዛብ ብቻ ናቸው በላትኞች እነሱም በላተኛ ነታቸው ጌታን እስኪ ቀብሉድረስ ነው። "የሚሰጥ በልግስና ይስጥ፤" ሮሜ 12፡8
ይህን ካልኩ የብቃል እናንት ቀጥሉ
ተባረኩ።

 **3** ዓመታት በፊት በ YaelD (8,060 ነጥቦች) የተመለሰ
ከ **3** ዓመታት በፊት የታረመ በ YaelD

?? ?? ???? ??? ? ??? ???? ?

ስለ አስራትም ይሁን ስለ መባ ያልከው ሁሉ መልካም ሆኖ ሳለ አንድም ግን አዲስ ኪዳን ላይ ያሉ አማኞች እንዲህ ያለውን የአስራትና የመባ ወዘተ ነገር ሲያደርጉ አለመታየቱና አንዷም አለመታዘዙን ግን ዘንግተኸዋል። አብርሃም ያደረገውን ሁሉ እናድርግማ ካልን፤ እንግዲያውስ እንስሳትም ልንሰዋ ነዋ? ጉዳዩ አዲስ ኪዳን ያሉ አማኞች እንዴት ነው ገንዘብ የሰጡት የሚለው ላይ ነው እንጂ አብርሃም እንዲህ ሰጠ የሚለው አይደለም። ደግሞ አብርሃም እኮ አንድ ጊዜ ብቻ ነው አስራት ያወጣው። ስለዚህ እስቲ አዲስ ኪዳን ወንድሞቻችን እንዴት እንዳደረጉ ከእነርሱ እንማር። ማንም ገንዘብ አትስጡ ወይም ለጌታ ስራ አትተባበሩ አላለም። የአዲስ ኪዳን አሰራር በአስራት አይደለም ነው እየተባለ ያለው።

 3 ዓመታት በፊት በ ስም-አልባ አስተያየት ተሰጥቶበታል

?? ?? ????

yes it is not; in new testment we should be giving it all. if we can't give 100% let us start with 10%is that so bad?

 3 ዓመታት በፊት በ ስም-አልባ አስተያየት ተሰጥቶበታል

???? ????

We should not suppose to waste our lives doing religious rituals! We should learn to do things fromthe h eart. Only that which comes from the heart has any value at all before the eyes of the Lord.We should n ot produce spiritually dead people who only mechanically function and do what theyare told to do. This i s not the new testament spirit. And can you tell me the justification for givingmoney to a church that ha s already thousands of dollars in its bank account? It is absolutelynonsense! The money is to be invested on the lives of the poor and the missionary and not just bedeposited in a bank! I can tell you for sure th

e Lord will definitely start shaking the foundations ofmany current churches which have based their hop es on the tithes of there members rather thanon God himself. Every aspect of the church that is not buil t on and by the Lord will crumble untilthe unshakable foundation is left i.e. the Lord himself!

3 ዓመታት በፊት በ ስም-አልባ አስተያየት ተሰጥቶበታል

?? ?? ???

"yes it is not; in new testment we should be giving it all. if we can't give 100% let us start with10% i s that so bad?"

Brother/sister, it is not so bad,but why not we start with 15% or 20% or even 5%? Why is 10% ago od start while we are told to give as genereoiusly as it pleases us. GENEREOUSLY as it PLEASESus. Ca n you see these two words which seem contradictory? Practically they are not contradicting.Give what y ou believe is enough to the work of the gospel. But also give happily. What does thatmean? The work of the gospel needs a lot of money....so, what ever you give is not enough! So don'tbe satisfied by the amo unt you give - even if you give 100% of your money, the work is stillunfinished! But to make your mind happy or to let people know that you give the 'lion's share' inthe church, don't make yourself suffer and give for the sake of your personal pride - give happily.What ever you give,
5% or 10% or 100%,.....do it happily.

3 ዓመታት በፊት በ ስም-አልባ አስተያየት ተሰጥቶበታል

?? ?? ???

ወንድሜ መገረዝም እኮ የተጀመረው በአብርሃም ነው። ሆኖም በአዲስ ኪዳን "ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም። ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዶች ደግሜ እመሰክራለሁ።" ይላል። ስለዚህ እከሌ እንዲህ አደረገ ብለን ስርዓትን እንድንደግም አይደለም በአዲስ ኪዳን የተጠራነው። ነገር ግን የከበረውንና በመንፈስ የሆነውን የአዲሱን ኪዳናችንን ምንነት ተረድተን እንድንመላለስ እንጂ።

3 ዓመታት በፊት በ ስም-አልባ አስተያየት ተሰጥቶበታል

?? ?? ???

+ -

0 ድምጾች

ሰላም ለናንተ ይሁን!
አጭር መልስ ለሞክር መሰል፦

ይኸ የአስራትና የመስጠት ጉዳይ ያልተደፈረ ጥያቄ ነበር ያልተደፈረ መልስም ነው ያለው። ይሁንና ከላይ አንድ ወንድም የሰጡት የመጀመሪያው መልስ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ይመስለኛል። ምክንያቱም በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድም ስፍራ አስራት እንድንከፍል ምንም ዓይነት ትእዛዝ የለም። ይልቁንም ስለ መስጠት ይናገራል እነጂ። ታዲያ የሚገርመው ነገር ስለ መስጠት በሚናገርባቸው ክፍሎችም ቢሆን እንኳን በደስታና ከልብ በሆነ መልኩ እንዲሆን ያዛል እንጂ ግዴታ አድርጎ አያስቀምጠውም። ይህን ስል ታዲያ መስጠትን እየተቃወምኩ እንዳልሆነ ግልፅ ይሁንልኝ። የመጀመሪያ መልስ ሰጪ እነዳሉት መስጠት በአዲስ ኪዳን በዓለመ የሚደረግ እንጂ የእግዚአብሔርን እጅ ለመጠምዘዝ ወይም " አሁን ግዴታዬን ተወጣሁ! ኡፍ!" ብሎ ለመገላገል አይደለም።
ይሁን እንጂ አስራትን ወደ ቤተ ክርስቲያን ጎትተው በማስገባት የአማኙን ቤትና ኑሮ እየበዘበዙ ያሉት አንዳንድ "ባኪዎች" ጉዳይ አንድ ነገር ማለት ቢቻል መልካም ነው እላለሁ።